## «የብርቱካን ጉዳይ ትልቅ ጭጋግ ነዉ ፣ እንድትፈታ ትልቅ ግፊት እያደረግን ነዉ» ጆኒ ካርሰን !

ልዩ ዘገበ - አወደ ኢትዮጵያ
ሐምሌ 1 ቀን 2001

በአሜሪካ የዉጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የአፍሪከ ጉዳይ ሃላፊ፣ ጆኒ ካርሰን ባደረጉላቸዉ ጥሪ መሰረት፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አባላት ትላንት ማክሰኞ ሰኔ 30 ቀን ፣ በአሜሪካ ኤምባሲ ተገኝተዉ፣ ሰፊ ዉይይት ከአሜሪካን ባለሥልጣናት ጋር እንዳደርጉ ከአዲስ አበባ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ጀምሮ በተደረገዉ ስብሰባ፣ የአንድነት ምክትል ሊቀመንበር ኢንጂነር ግዛቸዉ ሽፈራዉ፣ የሕብረት መሪዎች ዶር መራራ ጉዲናና ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፣ የአረና ትግራይ ሊቀመንበር አቶ ገብሩ አሥራት፣ የኦሮሞ ፌደራሊስት ንቅናቄ ሊቀመንበር አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፣ የቀድሞ የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት ዶር ነጋሶ ጊዳዳና የቀድሞ የኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስቴር አቶ ሲዬ አብርሃ በተቃዋሚዎቹ ወገን የተገኙ ሲሆን፣ ከአሜሪካ ባለሥልጣናት በኩል ደግሞ ረዳት የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴሩ ጆኒ ካርሰንን ጨምሮ አምባሳደር ዶናል ያማማቶና በአሜሪካን ኤምባሲ የፖለቲካና የኢኮኖሚ አማካሪ ማይክ ጎንዛሌዝ ተገኝተዋል።

«የፓርላማዉ አሰራር እንዴት ነዉ ? ለመሆኑ የመረጣችሁን ሕዝብ በየጊዜዉ ሂዳቹህ ታነጋግራላችሁ ወይ ? የዲሞክራሲና የሰብዓዊ መብት መከበር ካለፉት አምሳ፣ አራባ አመታት ጋር ሲነጻጸር የተሻሻለ ይመስላቹሃል ወይ ? » የሚሉ ጥያቄዎች ጆኒ ካርሰን እንዳቀረቡ የደረሰን ዜና ሲያመለክት፣ የተቃዋሚ መሪዎችም በተጠየቁት ላይ ሰፊና መረጃ ላይ ያተኮረ መልስ እንደሰጡ ለማወቅ ችለናል።

የፓርላማዉን አሰራር በተመለከተ፣ የአንድነት ፓርቲ አባል የሆኑ ከአርባ የፓርላማ ተመራጮች አንድነትን ወክለዉ እንዳይንቀሳቀሱ መታገዳቸዉን ኢንጂነር ግዛቸዉ ሽፈራዉ ሲገልጹ፣ የፓርላማ አባል የሆኑት አቶ ቡልቻ ደመቅሳ፣ ዶር ነጋሶ ጊዳዳ፣ ፕሮፌሰር በየነና ዶር መራራ «ወንበር ላይ መቀመጥ ነዉ ስራችን። የተቃዋሚዎችን ሃሳብ በአጀንዳ ማስያዝ አይቻልም» ሲሉ ፓርላማዉ ፍጹም አፈና ያለበትና አሳዛኝ መሆኑን አስረድተዋል።

መራጩን ሕዝብ በየጊዜዉ ማወያየቱን በተመለከተ ለተጠየቁት ጥያቄ የተቃዋሚ መሪዎች መልስ ሲሰጡ፣ እንኳን መራጩን ሕዝብ ማነጋገር ፣ እራሳቸዉ ተመራጮች በየወረዳዉ ሲሄዱ ከፍተኛ እንግልትና ወከባ በየክልሉ ሃላፊዎች እንደሚደርስባቸዉ አስረድተዋል። ገዢው ፓርቲ «በተመረጣችሁበት ወረዳ ሕዝብን የማነጋገር ጉዳይ የክልል አስተዳደር ጉዳይ ነዉ» በሚል ሽፋን ሆን ብሎ ችግሩን መፍትሄ ለመስጠት

ፍላጎት እንደሌለዉና በኢትዮጵያ የዲሞርካሲ ሥርዓት ግንባታ እንዳይፋጠን እንቅፋት እየሆነ እንዳለም ገልጸዋል።

የፓርላማ አባላት ከክስ ነጻ የሆኑ (Immunity ያላቸዉ) እንደሆነ ያስታወሱት ኢንጂነር ግዛቸዉ ሽፈራዉ፣ በደንበጫ ጎጃም ከወረዳዉ የፓርላማ ተመራጭ ጋር ሕዝብን ባነጋገሩበት ወቅት፣ እርሳቸዉና የፓርላማዉ አባል ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ መታሰራቸዉን በመገለጽ ነበር ምን ያህል የፓርላማ ተመራጮች ከመረጣቸዉ ሕዝብ ጋር የመነጋገር ችግር እንዳለባቸዉ ለአሜሪካኑ ባለሥልጣናት ያስረዱት።

ካለፉት አርባ አምሳ አመታት ጋር አሁን ያለው የዲሞክራሲ ሂደት ምን እንደሚመስል ለተጠየቁት ጥያቄ የተቃዋሚ መሪዎች ሲመልሱ በዲሞክራሲ ግንባታዉ አንጻር ወደ ኋላ እየተኬደ እንደሆነና አሁን ያለዉ ሁኔታ አፋጣኝ መፍትሄ ካልተሰጠዉ እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ አገሪቷ እየወደቀች እንደሆነ ገልጸዋል።

«በአጼ ኃይለስላሴ ጊዜ ሰላማዊ ሰልፍ ስንወጣ አንድም ሰዉ አልተገደለም። በምርጫ ዘጠና ሰባት 196 ሰላማዊ ዜጎች ሲገደሉ ከሰባት መቶ በላይ ሲቆስሉ እንዳየነዉ፣ በአሁኑ ጊዜ ሰላማዊ ሰልፍ መዉጣት አይቻለም። ከተወጣም ትርፉ መገደል ነዉ» ሲሉ ዶር ነጋስ ጊዳዳ ምን ያህል የዲሞክራሲ ግንባታ ሂደቱ እንዳሽቆለቆለ ያስረዱ ሲሆን አቶ ቡልቻ ደመቅሳ በተለያዩ አለም አቀፍ ድርጅቶች እንደሰሩ በማስታወስ «ወደነ ሞቡቱና ሞንባሳ የሚጠጋ አምባገነንነት እየተጠጋን ነዉ» ሲሉም ዶር ነጋሶ ባሉት ላይ አክለዋል።

«በኢትዮጵያ የሕግ የበላይነት እየታየ አይደለም» ያሉት ኢንጂነር ግዛቸዉ ድርጅታቸዉ ስምንት ጊዜ ስብሰባ ለማድረግ ጠይቆ እንደተከለከለ፣ በከፊታቸዉ አምሳ ስምንት ጽ/ቤቶች ዉስጥ ከፍተኛ ችግር እየደረሰበት እንደሆነና ሕግ መንግስቱ በሚፈቅደዉ መሰረት ሕዝብን ማወያየት እንዳልቻሉ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ገለጻ አድርገዋል። **የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳይን በተመለከተ የእኚህ ታላቅ ሴት መታሰር የፖለቲካ በቀል እርምጃ እንጂ በምንም አይነት መልኩ ሕግ የማይደግፈዉ እንደሆነ በመግለጽ ገዢዉ ፓርቲ የወሰደዉን እርምጃ አውግዘዋል።**

ማንኛዉ እስረኛ በዘመድ፣ በሃኪም፣ መጠበቃ፣ በመንፈሳዊ አባት መጎብኘት እንደሚችል የአገሪቱን ሕገ መንግስት አንቀጽ 21 ቢደነግግም፣ ፍርድ ቤት ተከታታይ ወሳኔዎችና ትእዛዞች ቢያስተላለፍም፣ የፍርድ ቤት ዉሳኔ ተንቆ ወ/ት ብርቱካን ሰዉ እንዳይጎበኛቸዉ እስከአሁን መደረጉ የገለጹት ኢንጂነር ግዛቸዉ፣ የአንድነት ፓርቲ ሊቀመንበር ከስድስት ወራት በላይ በግፍና በጭካኔ በጨለማ ቤት ዉስጥ እንዲቀመጡ መደረጉን፣ ምሬት ባለዉ ሁኔታ ነበር ለአሜሪካኑ ባለሥልጣን ያስረዱት።

ኢንጂነር ግዛቸዉ ሲያክሉም የሚቀጥለዉ የ2002 ምርጭ ሁኔታ በጣም እንዳሳሰባቸዉ፣ በስብሰባዉ የተወከሉት ድርጅቶች በምርጫ የሚያምኑ በሕጋዊና ሰላምዊ በሆነ መንገድ የሚታገሉ ቢሆንም ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በታሰሩበት ሁኔታ፣ በየክልሉና በየወረዳዉ ወከባዎች እየተደረጉ፣ ጽ/ቤቶቻቸዉ እየተዘጉ፣ ሕዝባዊ ስብሰባዎች እንዳይደረጉ እየተከለከሉ፣ አባሎቻቸዉ ወከባና እንግልት እየደረሰባችዉ በምርጫዉ የመሳተፉ ነገር እንደሚያስቸግራቸዉ አስረድተዋል።

የአሜሪካዉ ባለሥልጣን ጆኒ ካርሰን ከትላንታና ወዲያ ሰኞ ሰኔ 29 ቀን ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊን እንዳነጋገሩ ገልጸዉ ፣ የፊታችን የ2002 ምርጫ ዲሞክራቲክና ሰላማዊ እንዲሆን ያላቸዉን ተስፋ ግለጸዋል። **የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳይ ትልቅ ጭጋግ ስለሆነ በአስቸኳይ መፍትሄ መፈለግ እንዳለበት ለጠቅላይ ሚኒሰትር እንደነገሯቸዉና መንግስታችዉም በዚህ ረገድ ትልቅ ግፊት እንደሚያደርግ በስብሰባዉ ለተገኙት የተቃዋሚ መሪዎች እንደገለጹ ለማወቅ ችለናል።**

ፕሬዘዳንት ኦባማ በጋና አክራ፣ ጁላይ 11 ቀን ፣ በዲሞክራሲ፣ ልማትና የሰብዓዊ መብት ጉዳይ ላይ ሰፊ ንግግር እንደሚያደርጉ የገለጹት ጆኒ ካርሰን አሜሪካ በኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሥርዓአትን ለመገንባት የሚደረገዉን ጥረት እንደምትደግፍ አሳዉቀዋል።

ያለፈዉ ሳምንስት  በአሜሪካ የዉጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ከሂሊሪ ክሊንተን ቀጥሎ ሃላፊ የሁኑት ጃኮብ ሌዉ፣ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ በኢትዮጵያ እየጠበበ ያለዉ የፖለቲካ ምህዳር የኦባማ አስተዳደርን እጅግ እንዳሳሰበዉ፣ ከጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናው ጋር ባደረጉት ዉይይትም የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ጉዳይ በአፋጥኝ እልባት ማግኘት እንዳለበት አጠንክረዉ እንዳሳሰቡ ለጋዜጠኖች መግለጻቸዉ የሚታወስ ነዉ።